

# እንዴት አሸናፊ መሆን እንደሚቻል።

መሸነፍ ማለት መውደቅ ወይንም አለመቻል ማለት ነው። መሸነፍ ማለት የማሸነፍ ተቃራኒ ነው። በአለም አቀፍ ሆነ በማንኛውም ውድድር ውስጥ የሚወዳደሩ ተወዳዳሪዎች ሁሉ አላማቸው ለማሸነፍ ነው።

እኛም በዚህ አለም በምንኖርበት ጊዜ የእለት እለት ኑሮአችንን በአሸናፊነት ለመኖር ነው የምንጥረው። ሕይወት ማጣት ማለት ውዳቂ መሆን ወይንም ኑሮን ለመኖር አለመቻል ማለት ነው።

በኑሮህ አሸናፊ መሆን ማለት የተሟላ ኑሮ መኖር ማለት ነው። ታድያ የተሟላን ኑሮን ለመኖር እንዴት አሸናፊ ሆነህ መኖር እንደምትችል ማወቅ ያስፈልጋል።

ያውም ለእለታዊ ኑሮ ብቻ ሳይሆን ለዘለአለም!

አሰናካይ የሆነው ሴይጣን (ዲያቢሎስ) ወደዚህ ምድር የመጣው ለሰርቅ፣ ሊገል፣ ሊያጠፋ ነው። እሱ የሚፈልገው እኛ ሰዎች ተሸናፊዎች ሆነን እንድንቀር ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ ወደኛ የመጣው ሙሉ በሙሉ ሕይወት ሊሰጠን በኑሮአችንም አሸናፊዎች ሆነን እንድንኖር ነው። ማንኛውም የሞቱ የሃይማኖት መሪዎች ለምሳሌ ያህል ኮንፍሴክስ፣ መሐመድ፣ ቡድሀ፣ ክሬሽና ወ.ዘ.ተ. አንዳቸውም ከሞት አልተነሱም አሁንም እንደሞቱ ናቸው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ሞትን ድል አድርጎ ተነስቶአል። ደግሞም ኢየሱስ ወደዚህች ምድር የመጣው የሃይማኖት መሪ ለመሆን ሳይሆን ሕይወትን ለሰጥህና አሸናፊ እንደትሆን ሊያበቃህ ነው።

ለመጀመሪ ጊዜ በዚህ ምድር የኖረው ሰው ስሙ አዳም ይባላል። እርሱም በኑሮው እግዚአብሔርን ከመታዘዝ ፋንታ አሳሳቹን ዲያቢሎስን ታዘዘ። በዚህም ምክንያት ኃጢያትና ሞት ወደዚህ ምድር ሊመጣ ቻለ።

እግዚአብሔር የሕይወት ምንጭ ነው። አዳም የመጀመሪያው ሰው በዚህች ምድር በኖረበት ጊዜ ባለመታዘዙ በሠራው ኃጢያት ምክንያት የሰው ልጅ በሙሉ ከእግዚአብሔር እንዲለይ አደረገ።

ነገር ግን እግዚአብሔር ስለሚወደን አንዱን ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ወደዚህ ምድር ልኮ የኃጢያትን ዕዳ እንዲከፍልልን አደረገ።

ኃጢያት ተሸናፊ ውዳቂ እንድትሆን ወይንም እንድትጠፋ አድርጎህ ነበር። ይህም ማለት ኃጢያት ከእግዚአብሔር ለየህ። እግዚአብሔር ግን አንድያ ልጁን ወደዚህች ምድር የላከው ከኃጢያትህ ሊያድንህና በአንተና በእግዚአብሔር መሐከል ያለውን የጥል ግድግዳ ሊያጠፋልህ ነው።

ኢየሱስ በፍቃደኛነት ለአንተ ኃጢያት ሲል ተገረፈ፣ እጆቹና እግሮቹ በሚስማር ተቸነከሩ፣ በመስቀል ላይ አንዴና ለመጨረሻ ሞተ።

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የሞተው የሰው ልጆችን ሁሉ የኃጢያት ዕዳ ለመክፈል ነው። ደሙን በመስቀል ላይ ያፈሰሰው አንተን ከኃጢያት ነፃ ለማውጣት ነው። የየሱስ ደም ቅዱስ ደም ነው። ኢየሱስ ፍፁም አምላክ ነው። ፍፁም ሰው ነው። ኢየሱስ በተአምር በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ከድንግል የተወለደ ነው። ኢየሱስ ከሰው ዘር አባት ከሆነው ከአዳም በኃጢያት ከተገኘና ከሱም ዘር ፍሬ የተገኘ አይደለም። ኢየሱስ የመጣው ከአባታችን ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው። የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢያት ሊያነፃን የሚችል እውነተኛና የታመነ ነው። በፈሰሰው በክርስቶስ ኢየሱስ ደም ከኃጢያት

እንደተዋደህ ስታምንና ኢየሱስ ክርስቶስን እንደግል አዳኝህ አድርገህ ስትቀበል ከማየት ሌላ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘው ነገር የለም። ይህንንም እርምጃ ስትወስድ ለዘለአለም አሸናፊ እንጂ ተሸናፊ አትሆንም።

ወገኔ ሆይ እንግዲህ እስከዛሬ ተሸናፊ ካደረገህ ኃጢያት እራስህን ለጌታ ኢየሱስ በመስጠት አሸናፊ ሁን። ኢየሱስ ክርስቶስንም ወደ ሕይወትህ እንዲገባና ከኃጢያትህ እንዳያድንህ ጠይቅ። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል 'የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናል'። ይህን ጸሎት አሁን እንጸልይ።

የኔ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እኔ በሕይወት ውድድር ውስጥ አሸናፊ መሆን እወዳለሁ። እኔ አንተ በሕይወትህ በደምህ እዳዬን እንድከፍልህና ሞትን ድል አድርገህ ከመቃብር እንደተነሳህ አምናለሁኝ። ኃጢያቴን ይቅር ብለህ አድነኝ። እኔም ከዛሬ ጀምሬ ሕይወቴን ለአንተ አደራ እሰጣለሁ። በሕይወቴ ዘመን ወደ መንግስትህ ምራኝ። በምሞትበትም ጊዜ የዘለአለም ሕይወትን ስጠኝ። አሜን!

እንዴት አሸናፊ መሆን እንደሚቻል በበለጠ ለማወቅ ከፈለጉ ፡ እንዲሁም ነፃ የዚህን አይነት ተጨማሪ እትሞች ለሌሎች ለማዳረስ ከፈለጉ ከዚህ በታች በሚገኘው አድራሻ ፃፉልን።


**DICK HANDLEY**
**WORLD SERVICES® INCORPORATED**
**P.O. BOX "A" • DOWNEY, CALIFORNIA, 90241 • USA**